# ሳይንስ እና ሕይወት

ታሪኩ አባዳማ ሐምሌ 2001

ካለምንም መደበኛ ትምህርት ወይንም የሙያ ማሻሻያ ፣ የብቃት መለኪያ እና ስልጠና እገሌ ለመባል የሚበቃበት አገር ኢትዮጵያ ብቻ ይመስለኛል። አናጢ ሆኖ መኖሪያ ቤት ለመሥራት ወይም መካኒክ ሆኖ መኪና ለመጠገን መደበኛ ትምህርት የሚያስፈልግ አይመስለንም። ቤቱ ላያችን ላይ ቢደረመስ ወይም እንደ ነገሩ የተጠጋገነው መኪና ጎዳና ላይ ገትሮ ቢያስተጓጉለን ያንኑ ጠጋኝ ከመንደር ፍለጋ ደግመን ከመሄድ አናመነታም።

መንደር ውስጥ መርፌ የሚወጋ በተገልጋዩ ዘንድ ዶክተር የሚል ማዕረግ ይሰጠዋል። ይህን ሹመት ለመርፌ ወጊው በማጎናፀፍ መንደርተኛው በቀዬው በሽታ ዝር እንዳይል ማስፈራሪያ የተከለ ይመስለዋል። ማሽላ ማሳ መሀል እንደሚተከለው የወፎች ማስፈራሪያ። ሰአትና ቀን ሳያግደው በጠሩት ግዜ ጎራዴ የሚያክል መርፌውን ቀስሮ ከተፍ የሚለው ያ 'ዶክተር' የመንደሩ ጤና አለኝታ (health insurance) ሆኖ ይኖራል።

ይኼ ቀድሞ የነበረ ቢሆንም ዛሬ 'ኢኮኖሚው አሻቅቦ' እና ሰላሳ ሶስት 'ዩንቨርሲቲ' ተከፍቶም አልተለወጠም።

ይልቁንም በወያኔ ዘመን ስለጡን ባለዛር መንደሩን ወሮታል። 'አንቱ' የተባሉ ጠብደል ጎረምሶች በሽታ እንፈውሳለን ፣ ሀብት እናስገኛለን በሚል ያንኑ ዳካማ ዜጋ ያራቁታሉ ፣ ያንገላታሉ። ተሸፋፍነው ወጥተው ተሸፋፍነው የሚገቡት እነኝህ ባለዛሮች ተግባራቸው ሁሉ ልክ እንደ ጠ/ሚኒስትሩ ጓዳ ለጓዳ ነው። ፊት ለፊት አይታዩም።

መርፌ ወጊው 'ዶክተር' በመባሉ ኩራት ተሰምቶት ፣ የሚዋጥ እንክብል እና ሌላም ምክር ወደ መስጠት ይሸጋገራል። እግሬን ሸመቀቀኝ ፣ የተወጋሁበት ቦታ ቆሰለ አመረቀዘ ብለን አቶ ዶክተርን ማማረር አይዳዳንም። ታዲያ በዚህ የደቦ ማዕረግ የተስማማ የሚመስለው የወያኔው ጠ/ሚኒስትር 'የሰለጠነ ዶክተር አያስፈልገንም' ሲል ሰምተናል። ሰውየው አስራ ሰባት አመት ጫካ በመኖሩ ከሳይንስ ጋር ሳይናናቅ የቀረ አይመስለኝም።

ወዲህ ደግሞ ሰላሳ ሶስት ዩንቨርሲቲ ከፍተናል ይባላል። ተከፈቱ ከተባሉት አዳዲስ ዩንቨርሲቲዎች አጥር ጀርባ ቢዘልቁ ከተጣደ ንፍሮ ሌላ ምንም እንደሌለ የሚያውቅ ያውቃል። በሩ ላይ 'ዩንቨርሲቲ' ብሎ መለጠፍ ቦታውን የጥበብ ማዕከል አያደርገውም። ለመጠሪያ ከሆነ ግን መርፌ ወጊውም 'ዶክተር' ይባል የለ?

ታዲያ ሁሉም የወያኔ ዩንቨርሲቲዎች እንደ ኦፒዲኦ እንደ ብአዴን በብሔረሰብ ስም ነው የሚጠሩት። ወያኔ ወያኔ እንዲሸቱ። ወያኔ ስም ሲያወጣ ዝም ብሎ አይደለም። ዩንቨርሲቲ በብሔረሰብ ስም - የብሔረሰቡ ሕዝብ ድንቁርናን እስከወዲያኛው የተገላገለ ፣ ኑሮው ህይወቱ የተለወጠ እንዲመስለው። ወፎቹን ከማሽላ ማሳ ለማራቅ ገበሬው እንደሚተክለው ምስል ወይም በመርፌ ወጊ በሽታን እንደሚያስፈራራ የዋህ ዜጋ ሁሉ ማይምነትን በተገተሩ ወና ዩንቨርሲቲዎች እያስፈራራ እንዲኖር የተፈረደበት ህዝብ … 'ዩንቨርሲቲ' እያለ።

ይህ አይነቱ '… በመጫኛ ጣሏት' አይነት ግንባታ ግን ብዙ አይዘልቅም - ለምን ቢሉ ህዝባችን የተዘፈቀበት ቅጥ ያጣ ሁለንተናዊ ችግር በባዶ ህንፃ ጋጋታ የሚለወጥ አይደለምና። አብርሀም ሊንከን እንዳሉት ውሻ አምስት እግር አለው ብሎ መከራከር ይቻላል ፣ ጅራቱን ጭምር ቆጥሮ። ውሻ የመሆኑን ዕውነታ ግን አይቀይረውም። በወያኔ የዩንቨርሲቲ ሕንፃ ብዛት ድህነት ፣ በሽታ እና ስደት ልዩ መታወቂያችን ከመሆን አይለወጥም ለማለት ነው።

ዓለም በሁሉም የጥበብ መስክ መጥቆ በሄደበት የዛሬው ዘመን ፣ ወታደር ጠመንጃ አስቀምጦ የዕድሜ ልክ ፕሬዘደንት ፣ አማፂ ከጫካ ዘገር ሲሰብቅ መጥቶ ተቀናቃኝ የሌለው ጠ/ሚኒስትር ወይም ያሻውን መሆን የመድፈሩ ምስጢር ባጠቃላይ የስከዛሬው ፖለቲካችን ለብቃት እና ዕውቀት የሚሰጠው ቦታ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን የሚመሠክር ነው። ብዙዎቻችን ከዚህ አዝማሚያ ጋር ሙግት እንገጥምና ራሳችንን ያፀናናን ሲመስለን የፖለቲካ መሪዎችን ዶክተር ፣ ኢንጂነር ፣ ረዳት ፕሮፌሰር እያልን እናሞካሻለን። አዋቂ መሪ ፣ አስተዋይ መሪ ለማግኘት ወይም ለማየት ካለን ፅኑ ምኞት የተነሳ። በወታደር እና በጠመንጃ አምላኪ ጎጠኛ ልቡ የቆሰለ ህዝብ ፣ መላ ጠፍቶት የተማሩ ልጆቹን ድረሱልኝ እያለ የሚማፀንበት የጥሪ ኮድ ይመስለኛል። ዶክተር ፣ ኢንጂነር ፣ ፕሮፌሰር …።

ችግራችን በማዕረግ የሚፈታ አለመሆኑን ጠንቅቀው የሚያውቁ ግን ብዙ እንደሆኑ እገነዘባለሁ።

የማዕረግ ነገር ሲነሳ በባርሴሎናው ኦሎምፒክ ታላቅ ድል የተጎናፀፈችው ጀግናዋ ደራርቱ ቱሉ ፣ ሻለቃ የሚል ማዕረግ በተሰጣት ሰሞን - "ሻለቃ ሲሉሽ ምን ይሰማሻል?" ብሎ ጋዜጠኛው ቢጠይቃት "ያስቀኛል" ያለችው ነገር የልጅቱን ልባምነት የሚጠቁም መልስ ነበር። በሚያስቁ ማዕረጎች ከተወረርን ብዙ ዘመን አለፈ።

አሁን በምኖርበት አገር በተለይ በሙያ ነክ ሥራ ለመሰማራት ከመደበኛ ትምህርት ተጨማሪ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም (certified) መሆን ግድ ነው። ምስክር ወረቀት ለመጨበጥ ደግሞ ያለምንም የዘር ወይም ፖለቲካ ታማኝነት አስፈላጊውን ስልጠና መቀበል እና ተዛማጅ ህግጋትን ማጥናት ብሎም መመዘኛ ፈተና ማለፍን ይጠይቃል። የብቃት ማረጋገጫ አስፈላጊነት ያገልግሎቱን ጥራት ከማረጋገጥ በላይ የሸማቹ ወይም የተገልጋዩ ህዝብ ደህንነት እና ጤና ባግባቡ መርካቱን (health and safety concerns) ለማረጋገጥ ይረዳል። ልበ-ሙሉ ባለሙያ ለማፍራት ሁነኛ ዘዴ ነው። የሕግ የበላይነት በሰፈነበት የምዕራቡ አለም በሙያ ብቃት ማነስ የተፈጠረ ስህተት ከሕግ አኳያ ብዙ መዘዝ ያስከትላል።

እኛ ከሰው መርጦ ለሹመት ፣ ከንጨት መርጦ ለታቦት እያልን ቀምበራችንን እናጠብቃለን።

የጋዜጠኛው ማስታወሻን የፃፈው የቀድሞ የወያኔ ካድሬ በታሪኩ መግቢያ ላይ እንዳተተው በደርግ ዘመን ፕሬስ መምሪያ በጋዜጠኝነት ለመቀጠር ማመልከቻ አስገብቶ ከደብረዘይት አዲስ አበባ እየተመላለሰ ደጅ ሲጠና በቀጠሮ መጉላላቱን ፣ በመጨረሻም ‘ጎጃሜ’ ባለመሆኑ ሳይቀጠር መቅረቱ ቅሬታ እንዳሳደረበት ገልፁዋል። ይሁንና የጎጃሜነቷን መሥፈርት እሱና መንገድ ላይ የተዋወቀው አንድ ሌላ ማመልከቻ አቅራቢ የፈጠሩት የሽኩሽኩታ መፅናኛ መሆኑን ሁዋላ ላይ አምኗል። ተስፍሽ ያን ግዜ ልጅ ነበር ፤ የፅሁፍ ችሎታ ወይም ዝንባሌ አለኝ ብሎ ለራሱ ካረጋገጠ የሚቀረው ነገር ማመልከቻ ማቅረብ እና መቀጠር ነው ብሎ ቢገምት አይፈረድበትም።

ተስፋዬ እንደገለፀው የረባ ሥራ ልምድ ወይም መደበኛ ስልጠና ሳይሰጠው ጋዜጠኛ ብቻ ሳይሆን የጋዜጠኞች ሹም ለመሆን በቅቷል። በብጣሽ ወረቀት ፀድቆ በተላከለት ሹመት ጋዜጠኞችን የሚሾም የሚሽር አለቃ ሆኗል። ሙያው እና እልቅናው እጅግ ከባድ እንደነበር ባይክድም ወያኔን ለማገልገል ግን ዋናው ተፈላጊ ነገር ከታማኝ ሎሌነት በላይ የዘር ግንድ መለኪያ መሠረታዊ እንደሆነ ያደባባዩን በጆሮ ነግሮናል። ይሁንና ተስፋዬ በወያኔ የተሰጠው ማዕረግ እንደ ደራርቱ አስቆት እንደሆን አልነገረንም። እነ በፍቃዱ ሞረዳ እሱን ሲያዩ ይስቁ እንደነበር ግን አልደበቀም።

የጋዜጠኛ ነገር ሲነሳ ሳልነካው የማላልፈው ነገር አለ - ባለፈው ሰሞን አፍቃሪ ወያኔ ድረ-ገፆችን ስከፋፍት አሁን ዋሽንግተን ባለው የወያኔ ኤምባሲ ሕዝብ ግንኙነት ሥራ ላይ የሚገኝ ፣ ድሮ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ የደርግ ኢሰፓአኮ ኢሰፓ ልዩ ባለሟል የነበረ የወያኔ ሰርጎ ገብ ስለ ወያኔ ‘ዲሞክረሲ’ የፃፈው ጉዳይ። ፀሀዬ ደባልቀው በዚህ ግንቦት ሰባት ንቅናቄ ላይ ያነጣጠረ ፕሮፓጋንዳው እንዳተተው ‘ዲሞክረሲ በሂደት’ የሚመጣ እንጂ ባዋጅ የሚገኝ አይደለም ብሎናል። ብዙ አንባቢዎች ሰውዬውን ስለማያውቁት በረጅም ሀተታው የዘባረቀው ነገር ፈይዳ ይኖረው ይሆናል ብለው ሊገምቱ ይችላሉ። ፀሐዬ ደባልቀው በደርግ ዘመን ‘ዲሞክረሲ በትግላችን’ የሚለውን ድርጋዊ መፈክር በየውይይት ክበቡ እየዞረ ሲሰብክ እናዛጋ ለነበርነው ግን የድሮውን ዘፈን ባዲስ ኦርኬስትራ እያዜመ ከመሆኑ ሌላ ያቀረበው ነገር የለም። እሱ ድሮ ‘በትግላችን’ ዘንድሮ ‘በሂደት’ እያለ ሲገለባበጥ እኛ ስናዛጋ ይኸው እዚህ ደረስን።

የፀሐዬ ነገር የከነከነኝ ዛሬ ‘ሂደት’ እያለ በመዝፈኑ አይደለም ፤ ይልቁንም ባሰረጫው ሀተታ ላይ ሌሎች የወያኔ በኩር ባለሟሎች በጉዳዩ ዙሪያ እንደሚገልፁት ‘ዲሞክረሲ በሂደት’ ይመጣል ሲሉ ዋቢ የሚጠቅሱት አሜሪካንን መሆኑ ነው። የ‘ኢትዮጵያ ፈርስት’ ድረ ገፅ ባለቤት (እሱም ጋዜጠኛ ነኝ ነው የሚለው) በማያውቀው ቋንቋ ሳይቀር ይህንኑ እንደሚያላዝን ብዙ ግዜ ሳትታዘቡ የቀራችሁ አይመስለኝም።

ግልገሎቹም ሆኑ በኩር ወያኔዎች እንደሚሉት “ከዓመታት ባንድ ዘመን የአሜሪካ ሴቶች ድምፅ የመስጠት መብት አልነበራቸውም ፣ ጥቁሮች በባርነት ተገዝተው ነበር…” ወዘተ የሚሉ ምሳሌዎችን በመነካካት የሂደቱን ባህሪ ሊያሳዩን ይሞክራሉ። ወያኔ ያልተገነዘበው ጉዳይ ካለ አሜሪካ ከተመሠረተችበት ዘመን አንስቶ የሕግ የበላይነት በፅኑ መሠረት ላይ ቆሞ የቆየባት አገር መሆኑን ነው። ሴቶች የምርጫ መብት ቢነፈጉ በሕግ ተደንግጎ ፣ ጥቁሮች በባርነት ቢገዙ እሱም በሕግ ተፅፎ ነው። ሕገ መንግስቱ  ሴቶች ድምፅ እንዳይሰጡ ፣ ባርነት ሕጋዊ የይዞታ መብት መሆኑን ያረጋግጥ ነበር። ድሮ።

መሠረታዊው የአሜሪካ ሕገ መንግስት አተረጓጎም እንደሚያረጋግጠው - በሕገ መንግስቱ ተፅፎ ያለው አንቀፅ የሌሎችን መብት እንደሚጋፋ ውሎ አድሮ ሲረጋገጥ ወይንም የአንቀፁ መኖር ጥያቄ ውስጥ ሲገባ በሕግ አውጪው አካል ይመከርበታል ፣ ይሻሻላል ወይንም ይሻራል። በአሜሪካ ምድር ከጥንት እስከ ዛሬ ስልጣን ላይ የመጣ መንግሥት ቀዳሚ ተግባሩ ሕገ መንግስት መከበሩን ማረጋገጥ ነው። ምንም ይሁን ምን በሕግ ተፅፎ የወጣ ነገር በሕግ እስካልተሻረ ድረስ ሕጋዊ ነው። ይሄ በሂደት የመጣ ሳይሆን በሕግ የበላይነት መገዛት የዲሞክረሲ ቀዳሚ እርምጃ መሆኑን የሚያረጋግጥ ጉዳይ ነው።

የወያኔ ችግር ዲሞክረሲያዊ አሠራር ማለት በሕግ የበላይነት መገዛት መሆኑን መቀበል ካለመቻሉ ላይ ነው። ይህ ደግሞ ዲሞክረሲ ከወያኔ ተፈጥሮ ጋር ሊራመድ የማይችል መሆኑን በማያሻማ መንገድ ያመለክታል።

ትናንት የደነገገውን ህግ ቀለሙ ሳይደርቅ እየጨፈለቀ ወዲህ ደግሞ በየጋጣሚው 'ዲሞክረሲ በሂደት' ይመጣል እያለ ቢዘፈነልን ይሄ ተራ የአምባገነኖች ዝማሬ ከመሆን አይዘልም።

መገንጠልን የማዕዘን ድንጋይ አድርጎ አንቀፅ 39 ላይ የደነገገ እና አጀቢዎቹ በታደሙበት በሆታ ዕልልታ የፀደቀ የወያኔ ሕግ መኖሩን ብናውቅም ፣ ዛሬ እንደምናየው ተገንጣይ ደገፋችሁ ተብሎ በኦጋደን እና በኦሮሞ ህፃናት ፣ ሴቶች እና ደካማ አዛውንት ባጠቃላይ በሰላማዊው ህዝብ ላይ የሚካሄደውን ያላባራ ወታደራዊ ሰቆቃ እና የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ማስተዋል ይበቃል።

የምዕራቡን ዓለም ትኩረት ይስባል ብሎ ወያኔ በህገ መንግስቱ ያካተታቸው እንደ ተቃውሞ ሰልፍ ማድረግ ፣ ሃሳብን በነፃ መግለፅ ፣ በነፃ መደረጀት እና በምርጫ ተወዳድሮ ሥልጣን መያዝ አንቀፆች ጠዋት ማታ እየተጣሱ ብቻ ሳይሆን በንፁሐን ዜጎች ደም እየጨቀዩ ባለበት ምድር እንዴት ብሎ ወያኔ ከአሜሪካ የዲሞክረሲ ግንባታ ሂደት ጋር እራሱን ለማነፃፀር እንደሚንጠራራ አይገባኝም። የምርጫ ሳጥን እየገለበጠ የሕዝብ ድምፅ የሚሰርቅ የፖለቲካ ሀይል ስለ ዲሞክረሲ ሂደት ፣ ያውም ስለ አሜሪካ የዲሞክረሲ ግንባታ ሂደት ምን ማለት ይችላል?

ባለፈው ፅሁፌ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ወያኔ ሊገነባ የሚችለው በጎጠኝነትን ላይ ጎጠኝነትን ብቻ ነው - ብአዴን እያለ ፣ ኦፒዲኦ … ቅብጥርሴ እያለ። የጎጠኝነት ግንባታ ሂደት የመጨረሻ ግቡ ደግሞ አገር እና ህዝብ ማጥፋት ነው። ጎጠኝነት በህብረተሰብ ውስጥ የተቀበረ የጥፋት ዲማሚት ነው። በብሔራዊ አንድነቱ ፀንቶ የኖረን ህዝብ 'አንድ አይደለህም ፣ በጎጥህ ክተት ፣ ሲሻህ ተገንጠል' እየተባለ በደምፍላት በሚሰበክበት የወያኔ ፖለቲካ ስለ 'ዲሞክረሲ ሂደት' ለመናገር መድፈር አንድም አላዋቂነት አለያም ተራ ሸፍጥ ነው። ወይም ያላዋቂ - ሸፍጥ ብንለው ይሻላል መሰለኝ። ሁለቱ ባህርያት ሲቀላቀሉ ውጤቱ ማህበራዊ ተውሳክ ይሆናል። የወያኔ ኮክቴል።

ዲሞክረሲ ሂደት በሆነባቸው አገሮች በሳይንሳዊ ዘዴ ያልተመረመረ ፣ ያልተጠና ሀሳብ ፣ የተመሠከረለት ባለሙያ ባደባባይ ያልተቸበት እና ያልተተቸበት እውነት ለተግባር ቀርቶ ለውሳኔ አይቀርብም። ውጤቱ ፣ መዘዙ ፣ ወጭው እና ትርፉ ከህዝብ እና ከብሔራዊ ጥቅም አኳያ እንደ ጉዳዩ ክብደት ተሰልቶ በጥንቃቄ መደምደሚያ መድረስ ለአፍታ የማይታለፍ እርምጃ ነው። ሕይወት በእውነት ላይ ካልተገነባ በድቡሽት ላይ የተሠራ ቤት ያህል ነው።

ሳይንስ ዕውቀት ነው ፣ ዕምነት አይደለም። ሁለት ሲደመር ሁለት አራት መሆኑን ለማረጋገጥ  የማንም መልካም ፈቃድ አያስፈልግም። ዕውቀት የማይናወፅ ሀይል ነው። ተራራን የሚደረምስ ፣ በሰማይ የሚያበር - በምድር የሚያሽከረክር ሳይንስ ነው። ደስ ያለው የሚቀበለው ፣ የደበረው ገሸሽ የሚያደርገው ጉዳይ አይደለም። ጠመንጃ በታጠቁ ፣ ጡንቻ በነረቱ መጠን የተናገሩት ሁሉ እውነት የሚመሥላቸው ጭፍን አምባገነኖች እና ባለሚሎቻቸው ብቻ ናቸው። አገር ከትናንት ዛሬ በሂደት እየሞተች መሆኑን እያየን 'በሂደት' ታድጋላችሁ እየተባለ ይላገጥብናል።

የአለም ኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ መግባቱን እና ኢትዮጵያ በዚህ የተነሳ ሊደርስባት የሚችለውን ተፅዕኖ አስመልክቶ በወያኔ ፓርላማ ትንተና ሲሰጥ መለስ ዜናዊ ያለውን ላስታውሳችሁ - እንደ መለስ አባባል “ቀውስ የገጠመው የአለም ኢኮኖሚ በውቅያኖስ ላይ የሚንሳፈፍ ትልቅ መርከብ አይነት ነው - ማዕበሉ የተነሳው ውቅያኖስ ላይ ነው ፣ የተናወጠውም ትልቁ መርከብ ነው - የኛ ኢኮኖሚ መንደር ወንዝ ላይ የሚንሳፈፍ ጀልባ አይነት ስለሆነ ቀውሱ ከቶ ሊያሰጋን አይችልም…” ቃል በቃል ባይሆንም የወያኔው 'ሊቅ' ለፓርላማው የሰጠው ዲስኩር ይህ ነበር። ውሎ ሳያድር ዶላር አጠረን ብሎ አይኑ ሲፈጥ ፣ ዕርዳታ ካልተሰጠን አለቀልን እያለ በየመድረኩ ሲወራጭ ላስተዋለው የሰውየው ignorance ከ arrogance ጋር ተዳቅሎ ምን ያህል የዘቀጠ አምባገነን መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም።

አዲስ አበባ በመብራት ፈረቃ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እያንቀላፋች መሆኑን እያየን 'ለጎረቤት የሚተርፍ መብራት ነገ እናፈልቃለን' ሲሉን መጃጃል የሚከጅለን ጥቂት አይደለንም። ግቤ ፕሮጀክት …ቅብጥርሴ እያሉ።

ሳይንስና ህይወት - እውነት እና ህይወት። እውነቱ እና ሳይንሱ ሀ አገርህን አድን …ለ በሕግ ተገዛ ይሉናል። ከዚህ ሌላ በወያኔ ቅዠት ውስጥ ራዕይ የሚታየን ካለን የሠፈራችንን መርፌ ወጊ በግዜ ብንፈልግ ይሻላል። ዶክተር ዶክተር አያልን።